መጋቢት 1 ቀን 2004

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን

## ዋሽንግተን ዲሲ፤

ለቤተክርስቲያናችን አስተዳደር አስተዳዳሪ መላከ ምኅረት ቆሞስ አባ እስጢፋኖስ ባህሩ እና ለቤተክርስቲያናችን አስተዳደር ቦርድ፤

የእግዚአብሔር ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

እንደሚታወቀው በቤተክርስቲያናችን ለሰባት አመታት ስንታገልለት የነበረውን ችግር ለመፍታት ባደረግነው ጥረት አንደኛውን ምዕራፍ በምርጫ ዘግተን ሌላውንና ሁለተኛውን ምዕራፍ ደግሞ በሂደት ለመቅረፍና ለማስተካከል የተሰጣችሁትን አደራና ኃላፊነት በትጋት በመወጣት ሰላምን፣ ፍቅርንና መረጋጋትንና አንድነትን በምዕመናን መካከል ለማስፈን በዝግጅት ላይ ናችሁ ብለን እንገምታለን።

ውድ ወገኖቻችን ማንኛውም ሰው በተወለደበት ባደገበትና እትብቱ በተቀበረበት ሀገር ከቤተሰቡ ከወዳጅ ዘመዱና ከኅብረተሰቡ ጋር በሰላምና በፍቅር መኖር ፍላጎቱና ደስታው ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በሀገሩ ውስጥ በሚከሰተውና በሚፈጠረው ውዝግብ ሁከትና ችግር ሳቢያ ሰላም አጥቶ ከመሞትና ከመንገላታት ህይወቱን ለማዳን ሀገሩን ጥሎ በመጥፋትና በመሰደድ ሰላማዊ ኑሮን ፍለጋ በተገኘው አጋጣሚና ሁኔታ ከሚወደው ሀገሩ ይሰደዳል። በስራ በንግድና በእንግድነት ወጥተው ከሚመለሱት ሌላ ብዙዎች በተለያዩ ምክንያቶች ከሀገራቸው ቢወጡም ዋንኛውና ትልቁ ግን ከሙቶ ዘጠና ፐርሰንቱ በስደት ከሀገራቸው የሚወጡት ናቸው። ለዚህ ሁሉ ችግር መነሻ መሰረቱ በሀገሪቷ ውስጥ በሚከሰተው የፖለቲካ ቀውስ መሆኑ እየታወቀ የሃይማኖት አባቶቻችን ግን ይህንኑ ጉዳይ “ስሙን አታንሱት፣ ኃጢያት ነው፣ ዝም ብላችሁ በጭፍን በድንግዝግዝና በግብዝነት ተመላለሱ፤” እያሉ የሃገራችንን፣ የዕምነታችንንና የሀይማኖታችንን ጉዳይ እንዳንከታተል፥ የተሰደድንበትን ዋናውን ምክንያት እንዳናስብ፥ የሚገጥሙንን ችግሮቻችንን እንኳ እንዳንናገር፣ ይልቁንም በግልም ይሁን በጋራ መፍትሄ እንዳናፈላልግ ከማድረጋቸውም ሌላ በተለይ በቅርብ አመታት የጀመሩት ፈሊጥና ማሰናከያ አድርገው የሚጠቀሙበት ዘዴ ምንም ዓይነት ነገር ይሁን ብቻ ለእነርሱ ካልመሰላቸው እከሌ ፖለቲከኛ ነው እያሉ በማጥላላት ያለምንም መረጃ ሰውን/ምዕመኑን ያለሀጥያቱ ይኮንናሉ።

ሌላው ደግሞ ይበልጡን የሚያሳዝነን የሀይማኖት፣ የቤተክርስቲያን መሪና የምዕመናን ጠባቂዎች ናቸው፥ ብለን ተስፋ በምናደርግባቸውና በምናምናቸው አባቶች ኢትዮጲያዊነትን፣ ሃይማኖትንና እውነትን የካዱ፤ ይልቁንም በገሀድ የምናየውንና የምንመሰክረውን ጉዳይ አናይም አንመለከትም ብቻ ሳይሆን እኛንም አትዩ አትመልከቱ እያሉን፥ ዛሬም በሀገራችን፣ በህዝባችንና በቤተክርስቲያናችን የሚደርሰውን በደልና ግፍ እያዩ የማያዩ እየሰሙ የማይሰሙ ጆሮአቸውን በህዝቡ ላይ የደፈኑ ህሊናቸውንም ለራሳቸው የካዱ ናቸው ብንል እናንተን ከማስታወስ በቀር አታውቁትም አንልም።

ልብ እንደምትሉት ህዝባችን ባለፉት አርባ አመታት በተፈራረቁበት ገዥዎች በወታደራዊው አስተዳደር ዘመን በሙቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ህይወትን በቀጠፈ ሰቆቃ ያለፈና በብርቱ የህሊና ስቃይ ውስጥ የኖረ ዛሬም እጅግ በከፋና በላቀ ሁኔታ በስልጣን ላይ በሚገኘው ከአስከፊው የኢህአዴግ መንግስት እጅግ የከፋ የጭቆና አገዛዝ በተፈጠረበት የፖለቲካ ቀውስ ሽሽቶ ያመለጠ መሆኑን በጠላትነት ከቆሙትና ለገዢዎች ካደሩት በስተቀር ይህንን ሃቅ የሚክድ ህሊና ያለው ኢትዮጵያዊ ይኖራል ብለን አናምንም።

ከላይ ለማስረዳት እንደሞከርነው ቤተክርስቲያናችን የነዚህን መንፈሳቸው የተጎዳውን ወገኖቻችንን ህይወት መታደግ፣ መጠበቅና ማፅናናት የአባቶች ኃላፊነት ቢሆንም ባለመታደል ግን ይህንን የሚያደርጉ አባቶች ማጣታችን አሳዛኝ ነው። መንጋውን፣ ምእመናንንና ቤተክርስቲያንን እንዲጠብቁ የተመረጡ የእግዚአብሄር አይኖች ናቸው፤ ብለን የምንመካባቸው ካኅናትና የወንጌል አርበኞች፥ በዚህ ጊዜ በተለያዩ የመከፋፈያ ስሞችና መጠሪያዎች ምዕመኑን በመከፋፈል

ለራሳቸው ጊዚያዊ ተድላ፣ ቁሳቁስ፣ ስልጣንና ንዋይ በአደሩ አሳዛኝና አሳፋሪ አባቶች ተለያይተን፣ ተከፋፍለን፣ መሳቂያም ሆነን መኖራችን ሳይበቃ፥ አሁን ደግሞ በነዚሁ ስግብግብ ቁሳዊያን ጦስ፥ በየአጥቢያችን የምናየውና የምንታዘበው የንፁህ ምዕመናን መሳቀቅና መታመስ ሁላችንንም አንገት የሚያስደፋና ለጆሮም የሚሰቀጥጥ ነው።

ይህንን በመሳሰሉ አሳዛኝ ሁኔታዎች ውስጥ ዛሬም እያለፍን ቢሆንም፥ በሄድንበት፣ በደረስንበትና በምንኖርበት ቦታ ሁሉ የኢትዮጵያዊነት መለያ የሆኑ ባህሎቻችንን፣ ወግና ልምዳችንን፣ ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን፣ ምግቦቻችንን፣ ሌሎችንም አኩሪ ታሪክና ቅርሶቻችንን ይዘን በመሰደዳችን ለነዚህ ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችን መጠበቂያ ከሚሆኑን ተቋማት መካከል በስደተኛው ወገናችን ፍላጎት ጉልበቱን፣ ገንዘቡንና ውድ የሆነውን ጊዜውን መስዋዕት በማድረግ ቅዱስ ሚካኤልን የመሰሉ የእምነት ህንፃዎችን ማነፅ ችለናል።

ነገር ግን ይህንንም እናድርግ እንጂ በሌላ በኩል፥ እንደምንሰማውና እንደምንመለከተው ዴሞክራሲ በሰፈነበት ህብረተሰብና በአደጉ ሀገሮች ብንኖርም ቀድሞ እንደለመድነው ውሸት፣ ተንኮል፣ ማታለል፣ የግለሰብ መብት አለማክበር፣ ለህግ ባለመታዘዝና ህብረተሰባችንን በመናቅ በሚፈፀሩት ትርምስ በአንድነታችን ተባብረን፥ በልዩነታችን ተከባብረን፥ መኖር የሚያቅተን ከሶስተኛ ዓለም መሪዎቻችን በተማርነውና በቀሰምነው የስልጣን እስከሞት ፍልስፍና ተበርዘን፥ በድሮ በሬ የማረስ ልምዳችንን ለመጠቀም የምንቃጣ በመሆናችን ነውና ከዚህ ነውርና አሳዛኝ ድርጊት ብሎም በህዝብ ከመጠላት፣ ከመነቀፍና ከመዋረድ ፈጣሪያችን ይጠብቀን።

ባለፈው ህዳር ወር 2004 ወደዚህ አሜሪካን ሀገር የመጡት አቡነ ፋኑኤል የዋሽንግተን ዲሲና አካባቢ እንዲሁም የካልፎርኒያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው በሹመት ወደዚህ ከመጡ ይሄው አራተኛ ወራቸው ቢሆንም በነዚህ ጊዚያት ቤተክርስቲያናችን የምትጓዝበትን የመከራ ጉዞ እናንተም የምታጡት አይመስለንም። ይህንን ታሳቢ በማድረግ፣ ከመጀመሪያውኑ የዛሬ ሰባት አመታት ቤተክርስቲያናችን ይህን ከመሰለ ችግርና ውዝግብ ውስጥ የገባችው ከአቡነ ፋኑኤል ወደአገራችን ኢትዮጵያ መመለስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ብንገነዘብም ከላይ በመግቢያችን እንደገለፅነው የችግሩ ሁሉ መነሻና ተጠያቂ እርሳቸው ቢሆኑም የእርሳቸውን ወደ ጎን በመተው የውስጥ ችግራችንን ለማቅለልና ለመጨረስ በወሰድነው እርምጃ ግማሹን በምርጫ አስወግደን የቀረውን ደግሞ በሂደት እንፈጽማለን የሚል ተስፋ ነበረን።

ይህ በእንዲህ እያለ አሁን ደግሞ እንደገና ተመልሰው የዲሲና አካባቢው እንዲሁም የካሊፎርኒያ ግዛት ጭምር በአባ ጳውሎስ ሿሚነት የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስና የሲኖዶሱ አባል ሆኘ መጣሁ ያሉት አቡነ ፋኑኤል፥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በገለልተኛው ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ጣልቃ ገብተው የሚፈጥሩብንን ችግሮችን እና በእርሳቼው ምክንያት የሚገጥመንን የሰላም ማጣት፣ የቅዳሴ፣ የአምልኮትና የፀሎታችንን ጊዜ በአግባቡ ልንጠቀምና ልንፈጽም አልቻልንም። በዚህም የተነሳ በተፈጠረው የተቃውሞ ሰልፍና ሌሎችም ብዙ ውዝግቦች አቢይ ፆማችንን በአግባቡ መፈፀም ቀርቶ ቤተክርስቲያናችንን በሰላም ለመሳለም እንኳ አልቻልንም። በመሆኑም ከምዕመኑ (ከአባሉ) በተሰጣችሁ ኃላፊነትና አደራ መሠረት በአስቸኳይ የአቡነ ፋኑኤልን ጉዳይ ርምጃ እንድትወስዱና ፆም ፀሎታችንን በሰላም እንድንቀጥል በማለት ተቃውሞአችንን እንደሚከተለው እናቀርባለን።

**1ኛ/** ጊዜና ሁኔታው ፈቅዶልን የኢትዮጵያ ሲኖዶስ ጉዳይ በዕርቀ ሰላም ተፈጽሞ ቁርጥ ውሳኔ በምእመናኑ እስኪደረስ ድረስ አባላት በመንፈሳዊ ወይም በአስተዳደራዊ እየተባሉ በሚገለጹ የመሸንገያ ቃላቶች ሳይጫኑብን እስከዛሬ እንደቆየነው ሁሉ አሁንም በገለልተኝነት የመቆየታችን መብት ተከብሮ እንድንቆይና ቤተክርስቲያናችን ከዚህ በኋላ ያለ ምዕመኑ ፈቃድ ምንም ዓይነት የሲኖዶስም ሆነ የሀገረ ስብከት የሚባሉ እንግዶችንም ሆኑ ጉዳዮችን እንዳያስተናግድ፤

**2ኛ/** አቡነ ፋኑኤል አሁን በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ለምናየው አጠቃላይ ትርምስ ሁሉ ዋናው ምክንያት እርሳቸው ስለመሆናቼው የሚታወቅ ስለሆነ የእርሳቸው ወደ ቤተክርስቲያኑ መምጣት ለቤተክርስቲያናችን ከሚሰጠው ጥቅም ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን መሆኑንም ሁላችሁም እያያችሁ በመሆኑ ቤተክርስቲያናችንን ከከፋ ውድቀትና አደጋ ለመጠበቅ እንዲቻል እርሳቸው ወደቤተክርስቲያኑ እንዳይመጡ እንዲደረግልን።

**3ተኛ/** ቤተ ክርስቲያናችን ደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል ንብረትነቱ የማንም ሳይሆን የደብረ ምኅረት ቅዱስ ሚካኤል አባላት ብቻ መሆኑ ለህዝብ በይፋ እንዲገለፅ፥ በተጨማሪም ሁሉንም አባላት በሚያስተዳድረው የመተዳደሪያ ህጋችን (By laws) ውስጥ በማያሻማ ቋንቋ የአባላት ባለቤት መሆን በግልጽ ተጠቅሶ እንዲገባ፤

**4ተኛ/** ከዚህ በፊት በፍርድ ቤትም ብልሹ መሆኑ የተመሠከረለት የመተዳደሪያ ደንብ እስካሁንም ድረስ በሥራ ላይ የዋለው ያለአግባብ ብቻ ሳይሆን ህገ ወጥም በመሆኑ በተጨማሪም በአንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 32 ፊደል ተራ "ሐ" መሠረት ያለ  ምእመናን ተሳትፎና ዕውቅና ሥራ ላይም በመዋሉ፤ እነዚህም አንቀፆች የገለልተኝነትን መብትና ነጻነት የሚጻረሩ መሆናቸውን በድጋሚ እየገለጽን ከዚህ በታች የተገለፁት አንቀፆች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲቆሙና ከአገልግሎት ውጭም እንዲሆኑ በጥብቅ እናሳስባለን። እነዚህም አንቀጾች በመተዳደሪያ ደንቡ

ሀ/ አንቀጽ ሁለት ንዑስ አንቀጽ አራት ፊደል ተራ "ለ"

ለ/ አንቀጽ ሁለት ንዑስ አንቀጽ አምስት በሙሉ ፊደል ተራ (ሀ፣ለ፣ሐ) የተገለጹት ናቸው።

ስለዚህ ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ ከገንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለቤተክርስቲያናችን ደህንነትና ለምዕመናን ጥያቄ ቅድሚያ በመስጠት ፈጣን እርምጃ በአስቸኳይ እንድትወስዱና ለደብዳቤያችንም መልስ አንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንድትሰጡን እንጠይቃለን። በተጠየቀው የጊዜ ገደብ መልስ የማናገኝ ቢሆን ግን ለቤተ ክርስቲያናችን ሰላምና ደህንነት ስንል ሌሎችንም እስከዛሬ ድረስ አምቀን ከያዝናቸው ሌሎች ጉዳዮች ጋር ወደሚቀጥለው እርምጃ ለመሄድ የምንገደድ መሆኑንም በአክብሮት እንገልፃለን።

በመጨረሻም የተወላገደውን አቃንታችሁ፣ የከረረውን አላልታችሁ፣ የመረረውን አጣፍጣችሁ፣ ለቤተክርስቲያንችን አንድነትና ሰላም አስባችሁ፣ ጥያቄያችንንም በበጎ መንገድና ዓይን ተመልክታችሁ በቅንነት እንድትፈጽሙልን በትህትና እንጠይቃለን።

ወስብሃት ለእግዜብሔር

የቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ተቆርቋሪ ምዕመናን